1. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 19 በተጠቀሰው ታሪክ ላይ የዘኬዎስ ስራ ምንድን ነበር?
ሀ)ዓሳ አጥማጅ ለ)ቀራጭ ሐ)ሊቀካህን መ)ገበሬ

2. ቁመቱ አጭር የነበረው ዘኬዎስ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ለማየት በምን ዛፍ ላይ ወጣ?
ሀ)ሾላ ለ)በለስ ሐ)ዝግባ መ)ወይራ

3. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 19 በተጠቀሰው ታሪክ ሕዝቡ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ ለምን አንጎራጎሩ?
ሀ)ለምን ከኅጢአተኛ ቤት ገባ ብለው
ለ)ለምን ተአምር አያደርግም ብለው
ሐ)አጋንንትን ሲያወጣ አይተው
መ)ሁሉም

4. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 19 ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለመሰለው ምሳሌ እውነት ያልሆነው የቱ ነው?
ሀ)ሦስቱም ሰዎች በምናናቸው አላተረፉም
ለ)አምስት ምናን የተሰጠው ሌላ አምስት ምናን አትርፏል
ሐ)0ሥር ምናን ያተረፈው ሰው አንድ ምናን ተጨምሮለታል
መ) መልስ አልተሰጠም

5. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ውርንጫውን ለምን ትፈቱታላችሁ ለሚላቸው ምን እንዲመልሱ ነገረ?
ሀ)የኛ ንብረት ነው እንዲሉ ለ)ልንሸጠው ነው እንዲሉ ሐ)ጌታው ይሻዋል እንዲሉ መ)መልስ አልተሰጠም

6. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለኢየሩሳሌም ምን ተናገረ?
ሀ) መዳን እንደተደረገላት ይቅርም እንደተባለች
ለ)ሰላሟን ስላላወቀች እንደምትፈርስ እና እንደምትጠፋ
ሐ)ብልጽግና እንደሚመጣ እና ሕዝቦቿም ደስ እንደሚሰኙ
መ)ሁሉም

7. "ቤቴ የጸሎት ቤት ይባላል" ይህንን ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በየትኛው ቦታ እናገኘዋለን?
ሀ)ትንቢተ ኢሳይያስ ምዕራፍ 56:7
ለ)የሉቃስ ወንጌል 19:46
ሐ)ትንቢተ ኢሳይያስ 7:14
መ)ሀ እና ለ

8. በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 20 ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባስተማረው የወይን ባለቤት ምሳሌ ላይ ገባሮቹ የገደሉት ማንን ነበር?
ሀ)ከአገልጋዮቹ አንዱን ለ)የወይን ባለቤቱን ሐ)ሚስቱን መ)ልጁን

9. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዱቃውያንን ስለትንሳኤ ሙታን ሲያስተምራቸው ምንን ጠቅሶ ነው?
ሀ)እግዚአብሔር ለሙሴ የተናገረውን
ለ)ቅዱስ ገብርኤል ለዘካርያስ የተናገረውን
ሐ)ሙሴ ለፈርኦን የተናገረውን
መ)ሁሉም

10.ፈሪሳውያን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ለምን ስለግብር ጠየቁት?
ሀ)ማወቅ ፈልገው ለ)አመፅ ሊያስነሱ ሐ)በአነጋገሩ ሊያስቱት መ)ሁሉም

11. "ሁለተኛ ሞት የለባቸውም" ስለተባሉት ጌታ የተናገረው የቱ ነው?
ሀ) የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉ
ለ) የሕይወት ልጆች ናቸው
ሐ) እንደ መላእክት ይሆናሉ
መ) ሁሉም

12.ጌታ ለሐዋርያቱ ተጠበቁ ያላቸው ከነማን ነው?
ሀ) የባልቴቶችን ገንዘብ ከሚበሉ
ለ) በአደባባይ እጅ ሲነሱዋቸው ከሚወዱ
ሐ) ከሚጸሙ እና ከሚጸልዩ
መ) ሀ እና ለ

13.ጌታ ለሰዱቃውያን ከመለሰው ተነስተን ስለ ትንሳኤ ሙታን ምን ማለት እንችላለን?
ሀ) በምድር የተጋቡ በሰማይም እየተዋለዱ ይኖራሉ፣ ይበዛሉ
ለ) ሙታን በሚነሱበት ጊዜ እንደ መላእክት አያገቡም አይጋቡም
ሐ) በትንሳኤ ሙታን ጊዜ ስለ ባለትዳሮች ጉዳይ አልተወሰነም
መ) ትንሳኤ ሙታን በድንግልና ለኖሩ ነው እንጂ ላገቡ ሰዎች አይደለም

14.ዘኬዎስ ለበደለው ሁሉ ስንት እጥፍ እንደሚሰጥ ቃል ገባ?
ሀ) 2 ለ) 3 ሐ) 4 መ) 5

15.ሰዱቃውያን ማለት እነማን ናቸው?
ሀ) የአይሁድን ታሪክ ጽፈው የሚያስቀምጡ
ለ) ትንሳኤ ሙታን የለም የሚሉ
ሐ) የአይሁድ ካህናት
መ) የአይሁድ መምህራን

16.በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 19 ላይ ምናን ተሰጥቷቸው 10 እና 5 አትርፈው፣ 10 እና 5 ከተሞች ላይ መሾማቸው የምን ምሳሌ ነው?
ሀ) ባለ 10ሩ ሃብታሞች በመንግሥተ ሰማያት የሚኖራቸውን ክብር ማግኘቱን፣ ባለ 5ቱ በድህነት ሠርተው የሚኖሩ ሰዎች የሚያገኙትን ክብር ማግኘቱን
ለ) ባለ 10ሩ በእድሜ የገፉ ሰዎች በመንግሥተ ሰማያት የሚኖራቸውን ክብር ማግኘቱን፣ ባለ 5ቱ ወጣቶች የሚያገኙትን ክብር ማግኘቱን
ሐ) ለባለ 10ሩ ዐሥሩን ቃላት በመጠበቅ የሚገኘውን ክብር ማግኘቱን፣ ለባለ 5ቱ አምስቱ አዕማደ ምሥጢር የሚያስገኙትን ክብር ማግኘቱን
መ) ለ እና ሐ

17."የዮሐንስ ጥምቀት ከወዴት ናት?" ብሎ ጌታ በጠየቀ ጊዜ የካህናት አለቆችና ጻሕፍት ምን ብለው መለሱ?
ሀ) ከሰማይ ለ) ከምድር ሐ) ከወዴት እንደሆነች አናውቅም መ) መልሱ የለም

18.ጌታ ሐዋርያት ሰው ያልተቀመጠባትን የአህያ ግልገል እንዲያመጡለት የላካቸው ወዴት ነው?
ሀ) ቤተ ፋጌ ለ) ቤተልሔም ሐ) ቢታንያ መ) ሀ እና ሐ

19.ባለ አንድ ምናኑ አገልጋይ የምን ምሳሌ ነው?
ሀ) ተምሮ ሌላውን የሚያገለግል
ለ) ተምሮ ሳያስተምር የቀረ
ሐ) መክሮ አስተምሮ ራሱን አስመስሎ የሚያወጣ
መ) መልሱ የለም

20. "ላለው ይሰጡታል፤ ይጨምሩለታልም፤ የሌለውን ግን ያንኑ ያለውን ቅሉ ይወስዱበታል። " የሚለው ምን ማለት ነው?
ሀ) ለሀብታም ሰው ብር ይጨምሩለታል፤ ከድሀው ግን ይወስዱበታል
ለ) አእምሮ ላለው ምሳሌውን ይነግሩታል
ሐ) ጤና ለጎደለው ሕመም ይጨምሩለታል
መ) ሁሉም